# ”ምርኮ ፈጠነ፥ ብዝበዛ ቸኮለ”

**(ዴቭ ዳዊት)**

**August 31, 2017 01:14**

የአማራ ህዝብ የምንግዜም ጠላት የሆነው ወያኔ ትግሬ ”የቅማንት ህዝብ የማንነት ጥያቄ” በሚል ሽፋን በአማራዊው ላይ ከውስጥ ግንባር የከፈተበትን ጦርነት /Inner Front Warfare/ ሁለንተናዊ ገጽታ ከባለ አጀንዳው የትግሬ ህዝብ እና ቡድን እንዲሁም ከተላላኪውና ራሱን ”የቅማንት የማንነት ጥያቄ መፍትሔ አፈላላጊ ኮሚቴ” እያለ ከሚጠራው ቡድን አንፃር በመረጃ እና በማስረጃ ተደግፈን እንዲህ እንመለከተዋለን። መልካም ንባብ!!!



እንደሚታወቀው ወያኔ ትግሬ ሀገሪቱን በዘውግ ፌደራሊዝም አዋቅራለሁ ብሎ ሲነሳ ታሪካዊ እና ነባር ይዞታዎቻችንን በመቆራረጥ እና ለሌሎች በማቀራመት የተረፈውን ”የአማራ ክልል” በሚል ሰይሞታል። በዚህ ክልል ውስጥ ህዳጣን /Minority/ የሆኑ ሌላ ህዝቦች አብረው ከአማራዊው ጋር በሰላም ለዘመናት የኖሩ ሲሆን በፊትም ሆነ አሁን ያለምንም ጫና ባህላቸውን እና ቋንቋቸውን ያለመሸማቀቅ እንደሚጠቀሙበት አሌ የማይባል ሐቅ ነው።

ከዚህ ጎን ለጎን በባህሉ እንግዳ ሲመጣ እግሩን አጥቦ፥ የራሱን ማደሪያ ለእንግዳው ለቆ ለኖረው አማራዊ እነዚህ ህዳጣን /Minority/ ህዝቦች ራሳችንን በራሳችን እናስተዳድራለን ቢሉ ደስታችን ወሰን ቢያጣ እንጂ ግንባራችንን የሚያስቋጥረን አንዳች ነገር የለም፣ ሊኖርም አይችልም።

ነገር ግን ”የማንነት ጥያቄ” አለኝ በሚል ሽፋን ላለፉት ሃምሳ አመታት በሀገሪቱ ውስጥ የተጠፈጠፉ የሀገሪቱ ፖለቲካዎች የተቦኩበትን የፀረ-አማራ የጥላቻ እርሾን ይዞ ያውም ከመካከላችን በአባቶቻችን ርስት ላይ መነሳት ለእኛ ለአማራውያን አንድም አሜን ብለን የተደቀነብንን የህልውና አደጋ ተቀብለን እንደፍልስጤም ከዓለም ካርታ ላይ እየተፋቅን የምንጠፋበት አልያም እንደቀደሙ አባቶቻችን ”አማራ በርስቱ፥ አምላክ በመንግስቱ ሲመጡበት አይታገስም” ብለን በዋናነት የዘንዶውን ጭንቅላት ወያኔ ትግሬን ቆርጠን የምንጥልበት፤ እንዲሁም ተላላኪዎቹን የምናሳፍርበት እጅግ ወሳኝ እና ነገን እንደህዝብ በመኖር እና ባለመኖራችን ላይ የምንወስንበት ታሪካዊ ወቅት ላይ እንገኛለን። ስለሆነም ”የቅማንት የማንነት ጥያቄ” ተብሎ የመጣው አጀንዳ የቆመበትን ፀረ-አማራ መሠረት በማስረጃ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

### ”የቅማንት የማንነት ጥያቄ” እርሾዎች /Building Blocks/

”የቅማንት የማንነት ጥያቄ” ብሎ የተነሳው ቡድን ራሱን ያዋቀረው እና በቅማንት ማህበረሰብ ውስጥም ሆነ በመገናኛ ብዙሃን እያሰራጨ ያለው አስተምህሮ የሚያጠነጥነው በዋናነት በሶስት ፀረ-አማራ አስተሳሰቦች ነው።

1. የአማራን ህዝብ ብሔራዊ ህልውና በመካድ እና በማንቋሸሽ /Denial of Ethnic Amhara and Disdaining/፡- ”የቅማንት የማንነት ጥያቄ” የሚለውን አጀንዳ በዋናነት ከሚዘውሩት እና ኮሚቴውን በበላይነት ከሚመሩት መካከል ”አያቴ ነብይ ነበሩ” እያለ የሚናገረውና በጎንደር ከተማ የመድሐኒት መሸጫ መደብር ባለቤት የሆነው ነጋ ጌጡ ተሰፋዬ አንዱ ነው።ይህ ግለሰብ የአማራ ህዝብ እንደህዝብ እንደሌለ፤ ዘሩንም መቁጠር እንደማይችል ይልቁን ከኦሮሞ፣ ከአገው፣ ከቅማንት እና ከሌሎች የተውጣጣ /የተዳቀለ/ ህዝብ ክርስትና በሚባል የማቅለጫ ማሰሮ /Melting Pot/ ውስጥ ከገባ በኋላ ”አማራ” እንደተባለ እ.አ.አ በጁላይ 19, 2014 ዓ.ም. ለታተመው አዲስ አድማስ ጋዜጣ በሰጠው ቃለ ምልልስ ላይ እንዲህ በማለት ይገልፃል፡-

”አማራዎች የዘር መነሻችሁን ግለፁ ብንላቸው የዘር መነሻ የላቸውም። እኛ ግን ቅማንትን ስንገልጽ ከመጀመሪያው የዘር መነሻ ጀምረን ነው። ………… ከኦሮሞ፣ ከአገው፣ ከቅማንትና ከሌሎች ህዝቦች የተውጣጣ ህዝብ በክርስትና ምክንያት አንድ ብሔር ሆኖ አማራ ተባለ።” ይለናል። /http://www.addisadmassnews.com/index.php?option=com_k2&view=item&id=14554 መመልከት ልብ ይሏል።/

በዚህም ሳይወሰን ይህንን የመሳሰሉ በርካታ በመርዝ የተለወሱ ፀረ-አማራ ተረቶቹን “የቅማንት ህዝብ ታሪክ” በምትል ጥራዝ አሳትሞ አሰራጭቷል።

እንግዲህ በዚህ ሰው አስተምህሮ መሠረት አማራ የሚባል ዘሩን መቁጠር የሚችል ብሔር የለም። ስለሆነም ራሱን በአማራዊነት እየገለፀ ያለው ህዝብ ባህሉም ሆነ መሬቱ የራሱ ሳይሆን ተዳቅለው የፈጠሩት ህዝቦች በተለይም የቅማንት እንደሆነ የተናገረበትን እነሆ ከዚህ በታች እናያለን።




2. አማራን መጤ እና ወራሪ በማድረግ /The Settler-Indigenous Political Game/:-

ነብዩ አያቴ አንድ ምክር መከሩኝ:- ”ይሄን ህዝብ የምታስጠራው አንተ ነህ፡፡ ጊዜው ሲደርስ ያለፍርሃት ለብሄረሰቡ መብት ታገል፣ ስሙን እንደገና አንሳው፤ ያኔ የኛ ህዝብ ቋንቋውን ያሳድጋል፤ ማንነቱ ይከበራል፤ እንደገና ቅማንትነት ይነግሳል አሉኝ ” የሚለው ነጋ ጌጡ ተሰፋዬ ”Kemant Movement” በሚል ርዕስ በተዘጋጀ ዶክመንታሪ ፊልም ክፍል ሁለት ላይ ከ ዘጠነኛው ደቂቃ ሰላሳ ስምንተኛው ሰከንድ ጀምሮ ያለውን እኔ አሳጥሬ በዚህ መልኩ የፃፍኩት ሲሆን አንባቢ ግን ከታች የተጠቀሰውን ማስፈንጠሪያ /link/ በመጫን ሙሉ ቪዲዮውን ቢመለከተው የበለጠ ግንዛቤ ያገኛል።

ለማንኛውም የኮሚቴው ዋና ሞተር የሆነው ነጋ ጌጡ ተስፋዬ እንዲህ ይላል:- ”………..ቅማንትን ለማጥፋት የተራቡ አማራዎችን ከሌላ አካባቢ አምጥተው አሰፈሩ። አሁንም ቢሆን የቅማንት ሰዎች የመሬቱ ተጠቃሚ አይደሉም። መተማ እና አርማጭሆ ውስጥ የቅማንት ሰፋፊ የጥጥ እና የሰሊጥ መሬቶች ላይ ሰፍሮ እየተጠቀመ ያለው ቅማንት ሳይሆን አማራ ነው።ቅማንት ዕድሜ ልኩን ይዞት የኖረውን መሬት ማንም /አማራ/ ዛሬ መጥቶ ርስተኛ ሊሆን ስለማይችል መሬቱ ዞሮ ዞሮ የቅማንት ነው።” /https://www.youtube.com/watch?v=Hj9Wua4w6ng መመልከት ልብ ይሏል።/

እዚህ ጋር ይህ የነጋ ጌጡ ተስፋዬን አባባል ከወያኔ ትግሬ ማኒፌስቶ-68 ጋር ማነፃፀሩ አስተሳሳቡ ከአንድ ምንጭ እንደተቀዳ ለማየት ይረዳናል። ወያኔ ትግሬ የአማራ ህዝብ የትግራይ ህዝብ ጠላት ነው ባለበት ሰነዱ መሬትን በሚመለከት እንዲህ ነበር ያለው:-

”ባጠቃላይ ባሁኑ ጊዜ ትግራይ ነፃነቷን የተገፈፈች፣ መሬቷ ተቆራርሶ የተወሰዳባትና የተወሳሰበ ችግር የደቆሰው ሕዝብ የሚኖርባት ጭቁን ብሔር ናት።” /https://tassew.wordpress.com/tplf-manifesto-1968-e-c/ መመልከት ልብ ይሏል/።
ትናንት ትግሬ እንዲህ ብሎ ጀምሮ ነው ዛሬ የአማራ ታሪካዊ ይዞታዎችን በኃይል ከጎንደር እና ከወሎ በመውሰድ ወደ ትግሬ እንዲጠቃለሉ ያደረገው።

አማራዊው ወገናችን ሆይ!

እዚህ ጋር አንድ ነገር ከወዲሁ ልናሳስብህ እንወዳለን። ትናንት የቀደሙ አባቶችህ ይዞታ ከነበረው እና በአስራ አምስተኛው ክፍለዘመን በወረራ ከተያዘብህ መሬት እንደወራሪ እና ደን አቃጣይ እየተፈረጀክ ዝቅ ሲልም ”ሞፈር ዘመት

ገበሬ" እየተባልክ፣ በጉልበትህ ድካም ፥ በላብህም ወዝ ያፈራኸውን ሀብት እየተገፈፍክ ከቤኒሻንጉል፣ ከአርሲ እንዲሁም ከጉራፈርዳ እና ከወለጋ መሳደድህ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ብቻ ሳይሆን ዛሬም እየተፈፀመብህ ያለ የግፍ ተግባር ነው።

ይህ አልበቃ ብሎ ዛሬ፡-

"ያሳደግነው ጥጃ ለምለም ሳር አብልተን፣

ፈርገጥ ፈርገጥ አለ እኛኑ ሊረግጠን።"

ሆነና ነገሩ በትግሬ ሴራ እና በተላላኪዎቹ አስፈፃሚነት ከርስት ሀገርህ ከመተማ እና ከአርማጭሆ ገፋ ሲልም ከጎንደር ውጣ ልትባል ድግስ እየተደገሰልህ ነው። ነፃነትህን ብሎም ነገ እንደህዝብ የመኖር ተስፋህን ከፍ ብለህ ከሰማይ፥ ዝቅ ብለህም ከምድር አትፈልገው፤ ሁሉም ያለው በተሸከምከው መሳሪያ አፈ-ሙዝ ላይ ነው!!! ከዚህ በኋላ ክንድህ ብቻ ነው ህልውናህን የሚያረጋግጥልህ። ባሩድህ በወያኔ ትግሬ ግንባር ላይ ማረፍ ሲችል ብቻ ነው እረፍት ማግኘት የምትችለው!!!
እዚህ ጋር ግን ይህን ነውረኛ ግለሰብ /ነጋ ጌጡ/ በራሱ ቃል ወጥመድ ውስጥ ሲገባና ውሸቱ ሲጋለጥ እንደሚከተለው እናያለን። በጁላይ 19, 2014 ዓ.ም. ለታተመው አዲስ አድማስ ጋዜጣ በሰጠው ቃለ ምልልስ ላይ ወደታች ወርዶ እንዲህ ይላል፡- "ዋናው የቅማንት ታሪክ የነበረው አዲግራት ላይ ነው። ክርስትና በአክሱም በኩል ሲመጣ ቅማንቶች በአዲስ መጤ ሃይማኖት አንታለልም በማለታቸው ተከዜን ተሻግረው ወዲያ ማዶ ይሂዱ ተባለ። በዚያው ከተከዜ ወደዚህ በሶስት አቅጣጫ ፍልሰት /ከአዲግራት ወደ ጎንደር/ ሆነ።…………ስለዚህ ቅማንቶች የሰፈሩት ከሰሜን ተራራ አንስቶ እስከ ፓዌ ተራራ ነው።" http://www.addisadmassnews.com/index.php?

option=com_k2&view=item&id=14554 መመልከት ልብ ይሏል።/

እንግዲህ የአማራ ህዝብ ከዚያ ፈልሼ እዚህ ሰፈርኩ ብሎም አያውቅም፤ሊልም አይችልም። ምክንያቱም አሁንም ያለው ጥንት አባቶቹ በኖሩበት መሬት ላይ ነውና። "የነብዩ" ተስፋዬ የልጅ ልጅ ነጋ ጌጡ ግን ቅማንትን ትግሬዎች ክርስትናን አልቀበልም በማለቱ ከአዲግራት አስወጥተው ተከዜን አሻግረው እንዳባረሩት እየነገረን መልሶ አማራ በመሬቴ ላይ ሰፈረ ማለቱ ከጤነኛ ሰው የሚጠበቅ አይደለም።ርስትም አለኝ ካለ አማራዊውን ከመሬቱ ለማፈናቀል ከመከጀል ይልቅ አሳደዱኝ ያላቸውን ሰዎች ከተከዜ ማዶ አዲግራት ላይ ሄዶ መጠየቅ ነው ያለበት!!!

3. የአማራ ህዝብ የራሱ የሆነ ታሪክ፣ ትውፊትና እሴት የሌለው በማስመሰል /Labeling the Amhara People as uncultured and unsophisticated People/:-

   "የነብዩ" ተስፋዬ የልጅ ልጅ የሆነው ነጋ ጌጡ ተስፋዬ ለአዲስ አድማሱ ጋዜጠኛ አለማየሁ አንበሴ እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡- "የጎንደር ዘፈን እና እስክስታ የቅማንት ነው። የእነ ይርጋ ዱባለ ዘፈንና ዜማ የቅማንት ነው፤ ግን ሲዘፍኑ የቅማንትን ምድር ጎጡን አይጠሩትም። የሚጠሩት ቅማንት የሌለበትን ቦታ ነው። ………… ስለፋሲል እና ስለጎንደር መናገር የሚችለው ቅማንት ብቻ ነው። ሌላ ማንም ሊናገር አይችልም።" /http://www.addisadmassnews.com/index.php?option=com_k2&view=item&id=14554 መመልከት ልብ ይሏል።/

ይህ "ታሪክ እና ባህላችን ተሰርቋል" የሚለው ትርክት ምንጩ አንድ እንደሆነ እናይ ዘንድ ወያኔ ትግሬም በማኒፌስቶው ላይ ይህን አስፍሮ ነበር፡-

"ከዚህም በላይ የሚያኮራው የህዝባችን ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ እንዲደክምና ተዳክሞ እንዲጠፋ ወይም የአማራ ብሔር የገዥ መደብ ጥቅም እንዲጠበቅ የ፫ ሺ ዓመታት ታሪክና ባህላችን መመኪያቸውና መፎከሪያቸው ሆኖ ይገኛል። ይህ የታሪክ ስርቆት በአንድ በኩል ደግሞ ሰፊው የትግራይ ሕዝብ ታሪክ እንደሌለው ሕዝብ እንዲያስቆጥረው የተደረገ የመንግሥት መመሪያ ነው።" /https://tassew.wordpress.com/tplf-manifesto-1968-e-c/ መመልከት ልብ ይሏል/።

እንግዲህ አማራዊው ወገናችን ሆይ! ይህ ከወያኔ ትግሬ ጋር የሴራ ጋብቻ የፈፀመው ቡድን ትናንት ጌቶቹ ሲሉህ የነበረውን በቀጥታ በመገልበጥ እና በከፋ ሁኔታ በማጦዝ ነገ የአባቶችህ አጽም ካረፈበት፣እትብትህም ከተቀበረበት

ርስትህ ሊነቅልህ ብሎም እንደፍልስጤም ህዝብ በየስደተኛ ጣቢያው እንድትበተን ሊያደርግህ ቀናት እየቆጠረልህ ነው።

የተላላኪውን ቡድን ፀረ-አማራ አስተምህሮ ከላይ ካየነው ዘንዳ የሴራው ምንጭ የሆነው የትግሬ ቡድን አላማ እና ስልትን በአጭሩ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

"ለራሱ አያውቅ ነዳይ፥ ቅቤ ለመነ ለአዋይ" ይላል ህዝባችን በስነ-ቃሉ። ወያኔ ትግሬ እውን ለህዳጣን መብት የሚቆም ቢሆን በትግሬ ክልል የሚገኙ የሳሆ ብሔር አባላት ላይ የተፈፀመው እና አሁንም እየተፈፀመ ያለው የዘር ማጽዳት ዘመቻ በቆመ ነበር። በትግሬ ክልል ከጥንትም የምድሩ ባለርስት የነበረው የኩናማ ብሔር ራሱን በራሱ ባስተዳደረ፥ ቋንቋና ባህሉንም ያለተፅዕኖ ባሳደገ ነበር። በአክሱም እና አካባቢዋ የሚኖሩ ሙስሊም ወገኖች የአምልኮ ቤት /መስጊድ/ እንዳይኖራቸው ባልተከለከሉ ነበር /በዚህ አጋጣሚ የኦርቶዶክስ ቤተክስርቲያን በአክሱም መስጊድ አይሰራ ብላ አታውቅም ልትልም አትችልም። የቤተክርስቲያኗ ዶግማዋም ይሁን ቀኖናዋ ይህን እንድትል አይፈቅድም። "በአክሱም መስጊድ አይሰራም" የሚለው የትግሬ ህዝብ አቋም ነው!!! በተደጋጋሚም መስጊድ ሲሰራ እንደአንበጣ ሆ ብሎ እየወጣ የሚያፈርሰው ራሱ የትግሬ ህዝብ ነው። በእርግጥ አባታቸው ዮሐንስም ለእስልምና ሃይማኖት ስር የሰደደ ጥላቻ ስለነበረው ነው በላኮመልዛ /ወሎ/ የነበሩ አማራዊ ሙስሊም ወንድሞቻችንን ደማቸውን በጅምላ ያፈሰሰ።/

ታዲያ ወያኔ ትግሬ በባህርይው ለህዳጣን መብት የማይቆም ሆኖ ሳለ ትናንት ለዘመናት በሰላም በኖሩ ህዝቦች መካከል ጥላቻንና መቃቃርን መሠረት ያደረገ አስተምህሮ አስታጥቆ ከኋላ ደጀን በመሆን ለምን ተላላኪውን ቡድን አሰለፈ? የሚለውን ቀጥለን እንመለከታለን።

የፒልዙድስኪ መንገድ /Prometheanism or Prometheism/ "Any Euasian (Europe and Asia) Power would Crumble if its many minorities were empowered from without. "Josef Pilsudski. የፖላንድ ብሔርተኛ የነበረው ዮሴፍ ፒልዙድስኪ ሀገሩ ፖላንድ በራሽያ ግዛት ተይዛ በነበረበት ወቅት በራሽያ እና ጃፓን መካከል በ 1904-05 ጦርነት ሲካሄድ አንድ ሀሳብ ይዞ ወደ ጃፓን መንግስት ሄደ። ይኸውን ጃፓን በራሽያ ግዛት ውስጥ የሚገኙ ህዳጣን ህዝቦችን ብታስታጥቃቸው የራሽያን ኢምፓየር ከውስጥ ሆነው በመዋጋት እንደሚያፈርሱት ይነግራቸዋል። በሂደትም ይህ በፊት ለፊት ልትጋፈጠው የሚያስቸግርህን ኃይል በውስጡ ያሉ አነስተኛ አካላትን በራሱ ላይ እንዲነሳሱበት በማድረግ የምታዳክምበት እና የምታፈራርስበትን መንገድ ፒልዙድስኪ "ፕሮሜቲንዝም" ወይም "ፕሮሜታይዝም" ሲል ሰየመው።ስያሜውንም ከግሪክ አፈ-ታሪክ ውስጥ እሳትን ከዜውስ ሰርቆ ለሰው ልጆች የሰጠው ፕሮሜተስ ነው የሚለውን መሠረት አድርጎ ነው።

ይህ ፕሮሜታይዝም የትግል ስልት ለረጅም ጊዜ በቲዎሪ የቆየ ቢሆንም ቀዝቃዛው ጦርነት በአሜሪካ ድል አድራጊነት ሲጠናቀቅ አሜሪካ የጆርጅ ኬነንን "Containment" ፖሊሲዋን በመቀየር በራሽያ ላይ የፕሮሜታይዝምን ስልት ይዛ ትናንት በራሽያ ተፅዕኖ /Sphere of Influence/ ስር የነበሩ ሀገራትን በኔቶ እና በአውሮፓ ህብረት እንዲታቀፉ በማድረግ የራሽያን ከባቢያዊ ተፅዕኖ ማጥበብ እና ራሽያንም መክበብ ጀመረች።በዚህም ሳይወሰን በ 2008 ዓ/ም በአሜሪካ ተፅዕኖ ስር ያለችውን ጆርጂያን በመገፋፋት አብዛኛው ነዋሪዋ በዘር ራሽያዊ የሆኑባትን በራሺያ በር ላይ የምትገኘውን እና ራሽያ ብቻ እንደሀገር እውቅና የሰጠቻትን ደቡብኦሴቲያን አስወረረች። ፑቲንም የቤጂንግ ኦሎምፒክ የመክፈቻ ስነ-ስርዓትን በስቴዲየም ተገኝቶ እየተከታተለ እያለ በጠባቂው በኩል የደቡብ ኦሴቲያ መወረር በካሜራ ፊት ተነገረው። ፑቲንም ከስቴዲየም አቋርጦ በመውጣት ራሽያ ጆርጂያን በሰዓታት ውስጥ እንድትወር ሲያስደርግ የጆርጂያው ፕሬዝደንት በአለማቀፍ ሚዲያዎች ፊት ቀርቦ በድንጋጤ ክራቫቱን እያኘከ ታየ። በዚህም የአሜሪካ የፕሮሜታይዝም የትግል ስልት መቆም የሚችለው በጉልበት ብቻ እንደሆነ ፍንጭ ሰጠ። ለስድስት አመታት ያደባው የአሜሪካ መንግስትም በጆርጅ ሶሮስ ኦፕን ሶሳይቲ ኢንስቲትዩት በሰለጠኑ ካድሬዎቹ አማካኝነት ዩክሬንን ከራሽያ ካምፕ ወደ አውሮፓ ህብረት ካምፕ እናወጣለን ብለው መንግስት ገለበጡ። የዩክሬን ከራሽያ ካምፕ የመውጣት ሂደት አይቀሬ ከሆነ ራሽያ በክሬሚያ ሴቫስቶፖል የሚገኘው ስትራቴጂክ የሆነው የባህር ኃይሏ ቤዝ አደጋ ላይ መውደቁን የተገነዘበው የፑቲን አስተዳደር ክሬሚያን በሪፈረንደም አሳቦ ወደ ራሽያ እንድትጠቃለል አደረገ።ምስራቃዊው የዩክሬን ግዛት የሆነው የዶንባስ ክልልንም በማስታጠቅ ራሽያን እንድታዳክም በአሜሪካ የታጨችውን ዩክሬንን መልሶ አዳከማት። በአለማቀፍ ደረጃ ፕሮሜታይዝም ምን እንደሚመስል በዚህ ካየን ዘንድ ወያኔ ትግሬም ይህን ስልት እንደአቅሙ የራሱን ጥቅም በሌላው ኪሳራ ለማስጠበቅ ሲል ተጠቅሞበታል፤ እየተጠቀመበትም ነው።

ለምሳሌ የሀገሪቱን የንግድ እንቅስቃሴ በትግሬዎች ለማስወረር ይረዳው ዘንድ ለረጅም ጊዜ በንግዱ አለም የቆዩትን በተለምዶ ጉራጌ እየተባሉ በጥቅሉ ይታወቁ የነበሩ ህዝቦችን ጉራጌ እና ስልጤ በሚል ልዩነታቸውን ከፍ አድርጎ በማስጮህ ጉራጌ የተባለውን በመግፋት እና ስልጤውን በማቅረብ ይባስ ብለውም ስልጤዎች የዘር ሀረጋችን ከአረብ ነው እስከማለት ደረሱ።ስልጤውን በጉራጌው ላይ ካነሳሳው በኋላ ጉራጌው ወደጎን ሲገፋ እና ሲዳከም ተመልሶ የስልጤ ነጋዴዎችን በወንጀል በማነካካት እና በማጋለጥ /ባሌስትራ ወርቅ ነው ብለው ሽጡ ከሚለው ጀምሮ ኑሮን ያስወደዱት ስድስት የስልጤ ነጋዴዎች ናቸው በሚል ስም በመጥቀስ በማህበረሰቡ ውስጥ ሞራል እና ስነ ምግባር የሌላቸው በማስመሰል/ በሂደትም ስልጤውን በመምታት ሙሉ በሙሉ የንግዱ እንቅስቃሴ በትግሬዎች እጅ እንዲወድቅ አድርጓል።

በአማራዊው ላይም አሁን "የቅማንት የማንነት ጥያቄ" በሚል የተከፈተው የፕሮፓጋንዳይዝም የትግል ስልት አማራዊው ደሜ ነው ብሎ አቅፎ እና ደግፎ ያኖረውን የቅማንትን ማህበረሰብ እንወክላለን በሚሉ ተላላኪዎች አማካኝነት ከላይ ያየናቸውን ፀረ-አማራ አስተምህሮዎችን በመስበክ እንዲሁም የወያኔ ልሳን የሆነው ለወትሮው በትግሬ ቋንቋ አልያም በእንግሊዝኛ ጽሑፎችን የሚያወጣው ትግራይ-ኦንላይን የተባለው ድረ ገጽ ከ 2013 ጀምሮ ይህን መርዝ በአማርኛ ቋንቋ እየረጨ ይገኛል።

/http://www.tigraionline.com/constitutional-requirements-qimant.pdf

http://www.tigraionline.com/articles/kemant-amharization.html ለአብነት መመልከት ልብ ይሏል።/

በዚህም ሳይወሰን የትግሬ ዲቃላው አዲሱ ለገሠ "ትግሬ ከጎንደር ተባረረ" የሚለውን ተረት አስመልክቶ ለትግሬው ወይን ጋዜጣ አዘጋጆች አባዲ ገ/ስላሴ እና ሃይላይ ተከላይ በየካቲት 2009 ዓ.ም. ቃለ ምልልስ ሲያደርግ እንዲህ በማለት መርዙን ይረጫል፡- "በጣም የከፋውና አስቀያሚው ነገር የተጀመረው ቅማንት ላይ ነው።"

/http://hornaffairs.com/am/2017/03/09/addisu-legesse-andm-chairman-interview/ መመልከት ልብ ይሏል።/ ሲጠቃለልም ይህ "የቅማንት የማንነት ጥያቄ" በሚል ሽፋን ወያኔ ትግሬ በአማራ ህዝብ ላይ የከፈተው የፕሮፓጋንዳይዝም የትግል ስልት መዳረሻ ግቡ የአማራን ህዝብ ማዳከም እና ሀገር አልባ አድርጎ የአማራን ሀገር ከካርታ ማጥፋት እንዲሁም በሁሉቱ ወንዞች ማለትም በመረብ እና በባሮ ወንዞች መሀል /Intermarum/ የምትዘረጋውን የትግሬ ሀገር እውን ማድረግ ነው።

አማራዊው ወገናችህ ሆይ!

በመጨረሻም እንዲህ ልንልህ ወደድን፡- በዚህ አናርኪክ አለም ውስጥ ህልውናህን አስጠብቀህ ልትኖር የምትችለው በክንድህ ብርታት ብቻ ነው!!! አንተ በሁለት እግርህ ለመቆም ስትውተረተር አለም "አሸባሪ"፣ "ፅንፈኛ" ሊልህ ይችላል፤ ነገር ግን ተሳክቶልህ በሁለት እግርህ ስትቆም ትናንት የፈረጀህ መልሶ ይሸልምሃል፥ ደግሞም ያሞካሽሃል። በቃ ይሄ የምንኖርበት አለም ያልተፃፈ ህግ ነው። ትናንት የኢርጉን እና ሃጋናህ አባል የነበረውንና ለህልውናው የታገለውን ሜናኪም ቤግንን አሸባሪ ያለች አለም፥ ተሳክቶለት እስራኤልን እንደሀገር አቁሞ ሲመራ ተሽቀዳድማ የኖቤል ሽልማት የሸለመችው ይህችው ትናንት የፈረጀችው አለም ናት። ትናንት የግቢህ አጥር ሲነቀነቅ ቃትህን ስበህ ቢሆን ኖሮ ዛሬ የቤትህ ምሰሶ ስሩ ባልተማሰ ነበር። ከትግሬ ጋር እጅግ በጠበበ ዕድል እንኳን አብረን ልንኖር እንደማንችል መሽቶ በነጋ ቁጥር በተግባር እያሳዩን ነው። ስለሆነም አማራዊ የሆንን ሁሉ ለህልውናችን እና ለርስት ሀገራችን ስንል እጅ ለእጅ ልንያያዝ፣ ልንደጋገፍ እና በሁሉም ረገድ በምንችለው መንገድ ሁሉ ወያኔ ትግሬ ላይ ልንዘምት ዛሬ ግድ ይለናል።

ግዮናዊው የአማራ ሀገር በልጆቹ ደም ይከበራል!!!

ቸር እንሰንብት!